# የኢየሱስ ምሳሌዎች(9)

በኢየሱስ የተነገሩት ምሳሌዎች በሙሉ ምድራዊ ሰዎች በቀላሉ የሚረዷቸው፥ ሰሚዎቹ የሚያዋቋቸው፥ በእለት እለት ኑሮአቸው የሚገሟቸውና ከኑሯቸው ጋርም በቅርብ የተዛመዱ ሲሆኑ እነዚህን ነገሮች በመጠቀም ሰማያዊ እውነቶችን ለማስረዳት የተጠቀመበት የማስተማሪያ ዘዴ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምሳሌዎችን ሲጠቀም የምናየው ኢየሱስ ብቻ ሲሆን እነዚህም ምሳሌዎች በወንጌሎች ውስጥ ብቻ የተወሰኑ እንደሆነ ይታወቃል። ከወንጌሎችም ውስጥ አብዛኛውን የምሳሌዎች ክምችት የምናገኘው በመጀመሪያውና በሶስተኛው ወንጌል ማለትም በማቴዎስና በሉቃስ ውስጥ ነው።

ጌታችን ማስተማር በጀመረበት ጊዜ ምሳሌዎችን በመጠቀም ሳይሆን ፊት ለፊትና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ይናገር እንደነበረ ይታያል። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 እስከ 7 ድረስ ያለው የተራራው ስብከት በመባል የሚታወቀው ነው። ምናልባትም መልዕክቱን ለመቀበል ፈቃደኛ ባልሆኑትና በሆኑት መሃል በመለየት የተጠቀመበት ስልትም እንደሚሆን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ማቲዎስ 13፥11-16 ላይ ያለውን በመጥቀስ ይናገራሉ።

በአገራችን ሰምና ወርቅ በመባል እንደሚታወቀው ምሳሌዎችም ሁለት አይነት ገጽታ አላቸው። አንደኛው ማናቸውም ከሚነገረው ምሳሌ ጋራ እውቅና ያለው ሰው ሊረዳው የሚችለው ግልጽ የሆነው ሃሳብ ሲሆን ሌላው ደግሞ ጥልቅ የሆነ ስለ እግዚአብሄር መንግስት የሚያስተምር እውነትን ያዝላል።

አብዛኛውን ጊዜ ምሳሌዎች አንድ እውነትን ለመግለጽ የሚነገሩ ሲሆኑ በውስጣቸው ግን ብዙ የተለያዩ ሃሳቦች ስላሉ እነዚያን ሁሉ ለመረዳት በመሞከር ዋነኛ የሆነውንና ምሳሌው ሊያስተምረን የተነገበት ነገር ሲያመልጠን ስለሚችል ልንጠነቀቅ ይገባል።
ሌላው እነዚህንም ሆነ ሌሎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ምሳሌዎች ስናጠና ልናደርገው የሚገባን ትልቅ ጥንቃቄ ቢኖር ዶክትሪኖችን ምሳሌዎችን ብቻ በመጠቀም መመስረት ወደ ተሳሳተ ትምህርት ለመግባት ሰፊ ደጅን የሚከፍት ስለሆነ ዶክትሪን አድርጎ ለመያዝም ሆነ ለሰዎች ለማስተማር የተለያዩ ክፍሎችን በማገናዘብ ማጥናት ያስፈልጋል።

# ጥናት አንድ (ማቴዎስ 13፡1-23

የጥናት ዓላማ፡ ልባችን የእግዚአብሄርን ቃል መታዘዝ በተመለከተ ያለበትን ሁኔታ ራሳችንን ለመመርመር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ "ለእናንተ የመንግስተ ሰማይን ምስጢር ማወቅ ተሰጥቷችኋል፤ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም።" ማቴ 13፥11

1. የምሳሌው አድማጮች እነማን ነበሩ?
2. በቁ 1-9 ባለው ክፍል ውስጥ የምታያቸውን የመሬት አይነቶችና ዘሩን አቀባበላቸውን በተመለከተ በራስህ አማርኛ ገለጽ።
1. በቁ 10 ላይ ደቀመዛሙርቱ "ስለምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ" በማለት ለጠየቁት ጥያቄ የመለሰላቸውን መልስ አንተ እንዴት ትረዳዋለህ?
2. ቁ 11-17 ትን በማንበብ ኢየሱስ በምሳሌ ማስተማሩ ለሚከተሉት የመንግስቱን ነገር ለማስረዳትና ለሌሎቹ ለመሰወር የሚጠቀምበት ይመስልሃል ወይ? ከሆነስ እንዴት?
3. በ ቁ 19 ላይ ከሩው የተዘራውን የሚነጥቃቸው እንዳሉ ያሳየናል። እነዚህ ሰዎች የሚያስነጥቃቸው ነገር ምንድነው?
4. ቁ 20-21 ደግሞ በጭንጫ ስለሚመሰሉ ሰዎች ያሳየናል። በራሳችን ህይወት የዚህ አይነቱ ነገር እንዳይከሰት ማድረግ የምንችለው ነገር ምንድነው?
5. በዚህ ምንባብ ውስጥ ከተጠቀሱት የልብ ዓይነቶች በብዛት በአካባቢያችን የሚታየው የትኛው ዓይነት ልብ ይመስልሃል?
6. ከአራቱ ዓይነት መሬቶች ራስህን በየትኛው ውስጥ ትመድበዋለህ? የልባችንን ሁኔታስ መቆጣጠር የሚቻል ይመስልሃል ወይ? እንዴት?
7. እግዚአብሄር የወንጌሉን ቃል እንድታስተውልና የጌታን በጎነት ማየት እንድትችል ዓይኖችህን ለከፈተልህ ለመንፈስ ቅዱስ ሳምንቱን ሁሉ ምስጋና ስጥ። በተጨማሪ ደግሞ ልብህ ለጌታ ቃል የተከፈተና ምቹ እንዲሆን በጸሎት ቅረብ።

# ጥናት ሁለት (ሉቃስ 15:1-32)

የጥናት ዓላማ፡ እግዚአብሄር ወደ እርሱ በንስሃ የሚመለሱትን በደስታና በፍቅር አቀባበል እንደሚቀበላቸው ለመመልከት።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ "ልጄ ሆይ አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፤ የእኔ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው..." ሉቃስ 15፥31

1. ሉቃስ 15፥1-32 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ክፍል ውስጥ ሶስት ጠፍቶ መገኘትን የሚያሳዩ ምሳሌዎችን እናያለን። እነዚህን አጠር አጠር በማድረግ ሶስት ሰዎች በየተራ ይናገሩአቸው።
2. በቁ 2 ላይ ሃጥያተኞች የተባሉትን እናያለን። ፈሪሳውያን ስለነዚህ ሰዎች ስላላቸው አመለካከትና እግዚአብሄር ደግሞ ስለ እነርሱ ስላለው አመለካከት እነዚህ ሶስት ምሳሌዎች ምን ያስተምራሉ?
3. በቁጥር 2 ላይ ሃጥያተኞች በመባል ስም የተሰጣቸውና በዚያ የነበሩት ፈሪሳውያን ኢየሱስ እያስተማረ ስላለው ምሳሌ ሊኖራቸው ስለሚችለው አመለካከት ልዩነት ተናገር።
4. በእነዚህ ሶስት ምሳሌዎች ውስጥ እንደ እረኛ፥ እንደ ሴትና፥ እንደ አባት ሆኖ የቀረበው ማን ይመስልሃል? ለምን ይህን ማለት ቻልክ?
5. በተለይ ሶስተኛውን ምሳሌ ስንመለከት አባካኙ ልጅ ተመልሶ ወዳባቱ ሲመጣ ሊደረግለት ስለሚገባው አቀባበል የፈሪሳውያን አመለካከት ምን ሊሆን ይችላል ትላለህ?
6. ቁ 7, 10, 23 ትን ከቁጥር 28-30 ያሉትን ሃሳቦች አነጻጽር። የወንድምየው አነጋገር የእኛን ህይወት ሊነካ የሚችልበትን መንገድ በምሳሌ አስረዳ።
7. በአባካኙ ልጅ ታሪክ ሳይጨርስ ኢየሱስ ስለ ታላቁ ልጅ ይቀጥላል(ቁ 25-32)። በዚህ ክፍል ጌታችን ለአይሁድ መሪዎች ሊያስተላልፍ የፈለገው ተጨማሪ መልዕክት ምን ይመስልሃል?
8. 15፥31 ላይ የምናነበው የአባትየው አነጋገር ስለራሳችን ሊኖረን ስለሚገባን አመለካከት ምን ያስተምረናል?
9. ዛሬና በሳምንቱ ሁሉ እግዚአብሄር ሳይገባህ ስላሳየህ ፍቅር የምስጋና መስዋዕት አቅርብለት። አንተም ቢያንስ ለአንድ ሰው ፍቅሩን ለማካፈል ሞክር።

# ጥናት ሶስት (ሉቃስ 10፡25-37)

የጥናት አላማ፡ ርህራሄ ልናደርግላቸው የሚጠበቅብን እኛን ለሚመስሉት ብቻ እንዳልሆነና ከኛ ልዩ ለሆኑትም ማድረግ እንደሚኖርብን ለማስገንዘብ።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ኢየሱስም "አንተም ሂድና እንዲሁ አድርግ" አለው። ሉቃ 10፥37

1. ሉቃስ 10፥25-37 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ምንባብ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ነገር በራስህ አነጋገር ለመግለጽ ሞክር።
2. "ጎረቤቴ ማን ነው?" ብሎ ሲጠይቅ ይህ ህግ አዋቂ ምን ዓይነት መልስ የጠበቀ ይመስልሃል?
3. ጠያቂው አንተ ብትሆን "ጎረቤቴ ማን ነው?" ብለህ ለጠየከው ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠው መልስ ምን ዓይነት ስሜት ያሳድርብህ ይመስልሃል?
4. ቁ 30 ላይ የምናነበው አይነት ሁኔታ ማለትም እኛ አልፈን ለመሄድ የምንወስንባቸው ሁኔታዎች ያሉ ይመስልሃል ወይ? እስቲ ምሳሌዎችን በመስጠት ተወያዩባቸው።
5. ኢየሱስ ለምን ይመስልሃል አይሁዶች የሚጠየፉትንና የሚጠሉትን ሳምራዊ ሰው በዚህ ታሪክ ውስጥ ዋናውን ሥፍራ ሰጥቶ የተናገረው? (ቁ 31-33)
6. ሳምራዊው ሰው ይህንን ርህራሄ ማድረጉ አስከፍሎታል የምትለውን ዋጋ በዝርዝር ተናገር። እነዚህ የተዘረዘሩት ነገሮች ርህራሄውን ላለማድረግ ሊኖራቸው የሚችለው አስተዋጽዖ ምን ይመስልሃል?
7. "ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ።" ሲል ኢየሱስ ለህግ መምህሩ እያስተላለፈ ያለው መልዕክት ምንድነው?
8. ዛሬስ በእኛ ህይወት "ሂድ አንተም እንዲሁ አድርግ።" የሚለውን የጌታችንን ትዕዛዝ በሥራ ላይ ልናውል የምንችልባቸውን ሁኔታዎች ተናገር?
9. በፊታችን ባለው ሳምንት ውስጥ የክርስቶስን ፍቅር ለአንድ ሰው በተግባር የምትገልጽበትን መንገድ እየጸለይክ እርምጃ ውሰድ።

# ጥናት አራት (ማቴ 18፡21-35)

የጥናት አላማ፥ እኛ የተቀበልነውን ይቅርታ መጠን በመገንዘብ ሌሎችን ይቅር ማለት እንደሚጠበቅብን ለማሳየት።

የምናሰላስለው ጥቅስ፥ "እኔ እንደማርሁህ አንተም ባልንጀራህን ልትምረው አይገባህም ነበርን?" ማቴዎስ 18፥33

1. በዚህ ክፍል የምታያቸውን ተዋናኞች ዘርዝር። የሚካሄደውንም ሁኔታ በራስህ አነጋገር ግለጽ።
2. "በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ..." በማለት ነው ቁ 21 የሚጀምረው። ለጴጥሮስ ጥያቄ መነሻ የሆነው ነገር ምንድነው ትላለህ?
3. ጴጥሮስ የጠየቀውን ጥያቄ ስትመለከት ይቅርታ ማድረግን በተመለከት ስለነበረው አመለካከት ምን የሚነግርህ ነገር አለ?
4. "እስከ ሰባት ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት ጊዜ አልልም" ይለዋል። ኢየሱስ ይህንን ሲል ምን መልዕክት ለማስተላለፍ ፈልጎ ነው?
5. ቁ 23-27 ትን በማንበብ እግዚአብሄር ለአንተ ካደረገልህ ጋራ እንዴት ሊነጻጸር እንደሚችል አስረዳ።
6. በዚህ ውስጥ ጌታ ምን ትምህርት ለመስጠት የፈለገ ይመስልሃል? አንተስ በሚበድሉህ ላይ ሊኖረህ ስለሚገባው አመለካከት ምን ያስተምርሃል?
7. ቁ 28 ስታነብ ጌታው የማረውን የገንዘብ መጠንና እርሱ ለመማር እንቢ ያልውን የገንዘብ መጠን ስታነፃጽር ለራስህ ምን ትማራለህ?
8. በዚህ ምንባብ ውስጥ ይቅርታን አለማድረግ በእግዚአብሄር ፊት ምን ያህል የማይቀበለውና የሚጸየፊው ነገር እንደሆን የሚያሳይህ ክፍል የትኛው ነው?
9. የእግዚአብሄርን ይቅርታ ጥልቀት ማወቅና መረዳት ወንድምህን ወይም እህትህን ይቅር ለማለት ምን ያህል የሚረዳ ይመስልሃል?
10. ይቅር ማለትን በተመለከተ በራስህ ህይወት ልትተረጉመው የሚገባህ የተማርከው ነገር ምንድነው? ተጨማሪ ለወገኖች ልታስተላልፈው ያለ የተማርከው ነገር ካለ በዚህ ጊዜ አካፍል።

# ጥናት አምስት (ሉቃስ 18:1-8)

የጥናት አላማ፤ ሳንታክትና ሳናቋርጥ መጸለይ እንደሚኖርብን ለማስገንዘብ።
የምናሰላስለው ጥቅስ፤ "እግዚአብሄር ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮሁ ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን? እላችኋለሁ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል" ሉቃስ 18፥7-8

1. ቁ 1-5 ትን በማንበብ ይህ ክፍል ስለ መበለቲቱ የሚናገራቸውን ነገሮች ዘርዝር። ስለ ዳኛውስ የሚናገራቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው?
2. ለዚህች መበለት ለጥያቄዋ መልስ ለማግኘት ዋነኛ መሳሪያ የሆናት ነገር ምንድነው?
3. ይህ ክፉ ዳኛ የወሰደውን እርምጃ እንዲወስድ ያስገደደው ነገር ምን ነበረ?
4. በቁ 6-8 ላይ ስላሉት ሰዎች የጸሎት ዓይነት የምታያቸውን ነገሮች በሙሉ ዘርዝር።
5. ጌታ ይህንን ምሳሌ ሲናገር ሳንታክት ዘወትር እንድንጸልይ ነው። ታዲያ በቁ 8 ላይ የተጠየቀው ጥያቄ ከዚህ ሳይታክቱ ከመጸለይ ጋራ እንዴት ይገናኛል ትላለህ?
6. ተስፋ በመቁረጥ ጸሎትህን አቋርጠህ ታውቃለህ ወይ? ለምን? ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ለጸሎት ተስፋ የሚቆርጡባቸውን ምክንያቶች በአንድነት ተወያዩባቸው።
7. ይህ ምሳሌ ጸሎትን በተመለከተ ለአማኝ ያስተምራል የምትላቸውን ሃሳቦች በሙሉ ዘርዝር።
8. ይህ ክፍል የሚያስተምረንን እውነትና በሌላ ሥፍራ ደግሞ የለመነውን እንደተቀበልን እንድንቆጥር የሚነግረንን ሃሳብ እንዴት ታስታርቃቸዋለህ?
9. የአንተን ጸሎት በዚህ ምሳሌ ውስጥ በምናያት ሴት ሚዛን ስትመዝነው በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ ይገኛል?
10. በግል ህይወትህ ልትለማመደው ጌታ ያስተማረህን እውነት ለወገኖች አካፍል።

# ጥናት ስድስት (ማቴ 13፡24-30፣ 36-43)

የጥናቱ ዓላማ፥ ፍርድ ለእግዚአብሄር ብቻ መተው ያለበት ነገር እንደሆነ ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፥ "በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ።" ማቴዎስ 13፥43

1. በቁ 24-26 ውስጥ የተነገረውን ነገር በራስህ ቋንቋ በአጭሩ ተናገር።
2. ቁ 28-30 ትን በማንበብ ለተከሰተው ሁኔታ ባሪያዎቹ የሰጡት መፍትሄ ምን ነበረ? ባለቤቱ ያቀረበው አማራጭና ምክንያቱስ ምን ነበረ?
3. በምሳሌው ውስጥ የተጠቀሱት ነገሮች ምን ምን እንደሚወክሉ ቁ 37-39 ትን በመመርኮዝ ተናገር።
4. በዘሪው ምሳሌ (ማቴ 13፥1-23) እና በዚህ በዛሬው ክፍል ደቀመዛሙርቱ የሚወክሏቸው ሁለት የተለያዩ ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
5. ጌታችን ከግብርና ጋራ የተያያዙ ብዙ ምሳሌዎችን ተጠቅሟል። ለምንድነው ዘር ተዘርቶ የሚኖረው እድገትና የክርስትና ህይወት እድገት ተመሳሳይነት የሚኖራቸው?
6. በዚህ ዘመን ያለነው አማኞችስ ያለጊዜው እንክርዳዱን ለመንቀል የምንሞክርባቸው ሁኔታዎች ታያለህ? አንድ ወይም ሁለቱን ተናገር።
7. አንዳንዶች ይህንን ክፍል ቤተክርስትያን ሰዎችን ዲሲፕሊን ማድረግ የለባትም የሚለውን ሃሳብ እንደሚደግፍ ያስተምራሉ። ይህንን አስተያየት ከማቴዎስ 18፥15-15 ጋራ በማነጻጸር ተናገር። አስቀድመህ ግን ክፍሉን ሳታነብ የራስህን አስተያየት ተናገር።
8. ይህ ምሳሌ ስለ እግዚአብሄር ባህርይ ምን ያስተምርሃል?
9. ይህ ምሳሌ ለአማኞች የሚሰጠው ተስፋ አለወይ? አለ ካልክስ ተስፋው ምን እንደሆነ ተናገር።
10. ከዛሬው ትምህርት የተማርከውን ትምህርት ለወገኖች አካፍል።

# ጥናት ሰባት (ማቴ 24፡36-25፡13)

የጥናት አላማ፡ የጌታ ምጽዓት ድንገትና ባልታሰበ ሰዓት ስለሚሆን አማኝ ሁልጊዜ በተጠንቀቅ መጠበቅ እንደሚኖርበት ለማስገንዘብ።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ "እንግዲህ ቀኑን ወይም ሰዓቱን ስለማታውቁ ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ።" ማቴ 25፥13

1. በዚህ ምንባብ ውስጥ የምናነባቸው ምሳሌዎች የሚመሳሰሉበትንና የሚለያዩበትን ሃሳቦች ተናገር።
2. ማቴ 24፥36-41 የሰው ልጅ መምጣት እንዴት ነው ከኖህ ዘመን ጋራ የሚመሳሰልበት ምክንያት?
3. ኢየሱስ መብላትን፥ መጠጣትንና ማግባት መጋባትን ነው ወይ እየተቃወመ ያለው? ካልሆነስ ለማጉላት የፈለገው ሃሳብ በ25፥38,49 መሰረት ምንድነው?
4. በ24፥42-44 እንደ ሌባ፤ በ24፥45-51 ደግሞ በአደራ የሰጠውን ንብረቱን ለመረከብ የሚመለስን ሰው በማድረግ የራሱን አመጣጥ ያስተምራል። እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች እያንዳንዳቸው ስለ ጌታ መምጣት በተመለከተ የሚያጎሉት ሃሳብ ምንድነው? እኛንስ ምን ያስጠነቅቁናል?
5. 24፥36-51 ትን በማንበብ የጌታን መምጣት የደስታ ወይስ የሚያስፈራ ቀን ሆኖ ታየዋለህ? ለምን?
6. የሙሽራው መዘግየት የልባሞቹንና የሰነፎቹን ደናግል ልዩነት እንዴት ነው የሚገልጠው? ቁ 25፥6-12
7. ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ ተስፋ ከገባ ሁለት ሺህ ዓመታት አልፎታል። ይህ መዘግየቱ በአማኞች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ሁኔታ ተናገር።
8. እኛ በዚህ ሁኔታ ልባችን እንዳይዝልና በጉጉት ጌታችንን መጠበቅ እንድንችል ምን ማድረግ ያለብን ይመስልሃል?
9. የጌታህን መምጣት የምትጠባበቀው እንደ ልባሞቹ ቆነጃጅት በዝግጅትና በናፍቆት ወይስ እንደ ሰነፎቹ በግድየለሽነትና በዝለት? ሳምንቱን በዚህ ሃሳብ በጌታ ፊት ራስህን የመመሪያ ጊዜ አድርገህ ተጠቀምበት።

# ጥናት ስምንት (ሉቃስ 18፡9-14)

የጥናት አላማ፡ በእግዚአብሄር ፊት ለመጽደቅ የሚፈልግ ሰው በእርሱ ፊት ራሱን ማዋረድና በትህትና ማቅረብ እንጂ በራስ መታመን የትም እንደማያደርስ ለማስተማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ "ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ዝቅ ይላልና፤ ራሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ይላል።" ሉቃስ 18፥14

1. በመቅደሱ ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ሁኔታ ተናገር። የሁለቱን ሰዎች ልዩነት ያጎላሉ የምትላቸውን ነገሮች ዘርዝር።
2. የእነዚህን የሁለት ሰዎች ጸሎት ስታነብ በዚህ ዘመን የዚህ ዓይነቱ ልዩነት ሊኖር ይችላል ብለህ ታስባለህ ወይ? እስቲ ተጨባጭ በሆነ መንገድ አስረዳ።
3. ፈሪሳዊው ጸሎቱን ሲጀምር የእግዚአብሄርን ስም ጠርቶ ነው፤ ነገር ግን በጸሎቱ ለእግዚአብሄር ምን ያህል ቦታ ሰጥቶታል?
4. ፈሪስዊውና ቀራጩ ስለ እግዚአብሄር ያላቸውን አመለካከት በማነፃፀር ተናገር።
5. ይህ ፈሪሳዊ ምን ያህል ጊዜ ራሱን ከቀራጩ ጋራ ሲያወዳድር ይታያል? ራስን ከሰዎች ጋራ የማወዳደር አደገኛነት ምኑ ላይ ነው?
6. የቀራጩንና የፈሪሳዊውን ስለራሳቸው ያላቸውን አመለካከት አነጻጽር።
7. ፈሪሳዊው በህግ የታዘዙትን ነገሮች እንደፈጸመ ስለነዚያም በምስጋና እንደ ተሞላ ተመልክተናል። ህግን የጠበቀው እያለ ታዲያ ለምንድነው ቀራጩ እንደ ጸደቀ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን?
8. ዛሬስ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ መንፈሳዊ እንደሆንን ለማሰብ የምንፈተንባቸው ሁኔታዎች ያሉ ይመስልሃል ወይ? አብራራ።
9. በቁ 9 መሰረት የምሳሌው ትኩረት እነማን ላይ ነው? ለራስህ ከዚህ የምትማረው ትምህርት ምንድነው? ይህንን በተመለከተ ሌላ ለወገኖች የምታካፍለው ተጨማሪ ሃሳብ ካለህ ተናገር
10. አስተውለንም ሆነ ሳናስተውል ራሳችንን በማመጻደቅና ሌላውን በመናቅ ጌታን ባሳዘንባቸው ነገሮች ጥቂት ጊዜ ወስደን ራሳችንን በመመርመር በንስሃ እንቅረብ።

# ጥናት ዘጠኝ (ሉቃስ 12፡13-21)

የጥናት አላማ፡ የስግብግብነትን አደገኛነት ለማሳየትና በእግዚአብሄር ዘንድ ባለጠጋ የመሆንን አስፈላጊነት ለማጉላት።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ “የሰው ሕይወቱ በሃብቱ ብዛት የተመሰረተ ስላልሆነ፣ ተጠንቀቁ፤ ከስግብግብነትም ሁሉ ራሳችሁንም ጠብቁ”አላቸው። ሉቃስ 12፥15

1. ሉቃስ 12፥13-21 በአንድነት ይነበብ። ቀጥሮ 13-15 ትን በማንበብ ስለዚህ ወደ ኢየሱስ ስለመጣው ሰው የምታየውንና የምታስበውን ተናገር።
2. ኢየሱስ ለጥያቄው መልስ የሚሆነውን ይህንን ምሳሌ በሚናገርበት ወቅት ሰውየው የሚሰማው ስሜት ምን ይመስልሃል?
3. ጌታ ሲናገር በቁ 15 ላይ “...ተጠንቀቁ፥ ከመጎምጀትም ሁሉ ተጠበቁ።” እንዴት ነው መጎምጀት አደገኛ የሚሆነውና መጠንቀቅ ያለብን?
4. በቁ 16-19 ላይ ያለውን ባለጠጋ ሰው ከዚህ አንጻር ድርጊቱንና አመለካከቱን እንዴት ታየዋለው? ድርጊቱስ ከመጎምጀት ጋራ እንዴት ይያያዛል?
5. በዚህ ምንባብ መሰረት ብልጥግናን በተመለከተ በሰውና በእግዚአብሄር መካከል ያለውን ያስተሳሰብ ልዩነት አነጻጽር።
6. ይህ ምሳሌ ሰው ባለጠጋ እንዳይሆን የሚያስተምር ነው ወይ? ለምን ይህንን ለማለት እንደቻልክ አስረዳ።
7. ቁ 21 በእግዚአብሄር ዘንድ ባለጠጋ መሆን ሲል ምን ማለቱ ነው?
8. በእግዚአብሄር ዘንድ ባለጠጋ ለመሆን መውሰድ የሚኖርብንን አንዳንድ ተጨባጭ እርምጃዎች ዘርዝር።
9. በእግዚአብሄር ዘንድ ባለጠጋ እንደሆንክ ራስህን ታያለህ ወይ? ካልሆነ በንስሃ ወደ ጌታ በመቅረብ ሁኔታውን ለመለወጥ የግል ውሳኔ አድርግ ጌታም ይረዳሃል።

# ጥናት አስር (ሉቃስ 16፡19-31)

የጥናት አላማ፡ እግዚአብሄር በምድራዊ ነገር ሲያበለጥገን የሰዎችን ችግር ከማየትና ከመርዳት ፊታችንን እንዳንመልስ ለመማር። 1ኛ ጢሞ 6፥19-20
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ አብርሃምም"ሙሴንና ነብያትን የማይሰሙ ከሆነ አንድ ሰው ከሙታን ቢነሳ እንኳ አያምኑም" አለው። ሉቃስ 16፥31

1. በዚህ ባነበብነው ክፍል ውስጥ እየተካሄደ ያለውን ድራማ መሰል ሃሳብ በራስህ አነጋገር ግለጽ።
2. በምንባቡ ውስጥ የሚገኙትን ሰዎች በሙሉ ዘርዝር።
3. በሁለቱ ሰዎች መካከል ስለነበረው የኑሮ ልዩነት አጉልተው ሊያሳዩን የሚችሉትን ሃሳቦች ከተነበበው ክፍል ውስጥ ጠቁም።
4. ሕብረተሰቡ አንዳንዶች ለምን ደሃ እንደሚሆኑ ከሚሰጣቸው ሃሳቦች ጥቂቶቹን ተነጋገሩባቸው። አሁን ከተወያያችሁባቸው ሃሳቦች ውስጥ የትኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ብለህ ታስባልህ? ለምን?
5. ምሳሌውን በመመርኮዝ የሁለቱን ሰዎች ሁኔታ ከመሞታቸው በፊት፥ በቀብራቸው ጊዜና ከሞቱ በኋላ ሲሆኑ የምታያቸውን ነገሮች አነጻጽር።
6. ምሳሌው የተነገረበት ምክንያት አልዓዛር መንግስተ ሰማያትን የወረሰው ደሃ ስለሆነ፥ ባለጠጋው ሰው ደግሞ የሚሰቃየው በምድር ሃብታም ስለነበረ ለማስተማር ነው ወይ? አይደለም የምትል ከሆነ በእግዚአብሄር ቃል ደግፈው።
7. እግዚአብሄር ሰዎችን በቀላሉ ለማዳን ለምንድነው ሰዎችን ከሙታን በማስነሳት የማይጠቀምባቸው? በተአምራት ፈንታ ለመዳን መንገድ ሆኖ በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ነገር ምንድነው?
8. ይህ ምሳሌ የሃብታምና የደሃን ግንኙነት በተመለከተ ሊያስተምረን የሚችለውን እውነቶች ተናገር።
9. ከዚህ ክፍል ጌታ ለአንተ በግልህ የተናገረህና ለሌሎች ትምህርት ይሆናል የምትለው ነገር ካለ ተናገር።